# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

" ኢትግበሩ ቤተ አቡየ ቤተ ምሥያጥ።
ቤትየስ ቤተ ጸሎት ይሰመይ"

"የአባቴን ቤት መሸጫ አታድርጉት
ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል"
ቅዱስ ያሬድ



# ምኩራብ

በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ዐቢይ ጾም በገባ በሦስተኛው ሳምንት ምኩራብ በመባል ይታወቃል። ቅዱስ ያሬድ እነዚህን በዐቢይ ጾም ላሉ ሰንበታት ስያሜን ሲሰጥ ሦስተኛውን ምኩራብ ብሎ የጠራበት መሠረታዊ ምክንያት ቤተክርስቲያን በራሷ ሊኖራት ስለሚገባ ምግባርና አስተዳደራዊ ሥራት ወይም ለምእመኗ በተቋም ደረጃ ልታስተላልፈው ስለሚገባ መንፈሳዊ ማንነትና በተግባር ሊኖራት ስለሚገባ መገለጫ ጠብቆ ስለመቆየት የሚለውን አሳብ ይዞ ነው። እርግጥ ነው ይህንን አሳብ የቤቱን መመሰቃቀልና ፍጹም የተለየ ጾንፍ መያዝን ተመልክቶ መድኅን ዓለም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ ቤተ መቅደስን ሲጎበኝ ሙሉ ለሙሉ የመገበያያ ቦታና የመሻሻጫ ቦታ ሆኖ ተመለከተ ንብረታቸውንም ገለበጠባቸው ዮሐ 2፥13 - 19። ቅዱስ ያሬድም በጥቅሉ ከላይ የጠቀሰውን የጌታን ድርጊት ይዞ ከዐቢይ ጾም ሳምንታት አንዱ ለሦስተኛው ምኩራብ ብሎ ሰይሞታል።

በዋናነት በዚህ ሳምንት ስለ ቤተ መቅደስ ወደ ተፈጠረበት ወይም ወደ ተዘጋጀበት ዓላማ ሳይሆን መቅረት ቢወራም ቢነገርም በሌላም በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያን ስላላት ልዕልናና ክብር የጌታ ሚስቱ ስለተባለች ቤተክርስትያን ፍጹም ሰማያዊ ክብርም ይነገራል። ራሱ ቅዱስ ያሬድም በድጓው "ለቤተክርስቲያን ልዑል ሐነፃ በጽድቁ ሐወጻ እምነ ፀሐይ ይብርሳ ገጻ" ብሎ ተናግሮላታል። ወደ አማርኛ ሲመለስም ልዑል ቤተክርስቲያንን አነፃት በጽድቁም ጎበኛት ከፀሐይ ብርሃንም ፊቷ የበራ ነው ብሎ ቤተ ክርስቲያን ስላላት ክብር ከፍ ከፍ ያለ እንደሆነ በምልዐት፣ በጥብዐት፣ በላዕላይ መንፈስ ሆኖ ተናግሮባታል። ስለዚህ በአጠቃላይ በሦስተኛው ሳምንት የሚጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሆና እንድትቀጥል በውስጧ የሚገኙ በየትኛውም ማዕረግና ድርሻ ያሉ ሰዎች ሊፈጽሟቸው ስለሚገባ ድርጊት ጥንቃቄ ሊኖረው ስለሚገባ አካሄድ ያሳያል ያን በማያደርግ ላይ ባለቤቷ ክርስቶስ በመዓቱ ሊመጣ እንደሚችል ያሳየበት ትምህርት ነው።

ሐዋርያትን ጅራፍ አዘጋጁ አላቸው። ከዚያም የሚጋረፈውን እየገረፈ አስወጣ። እርግጥ ነው መጽሐፍ የሚለው "ጅራፍን አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አስወጣቸው" ዮሐ 2÷15 የጭፍራን ለአለቃ መስጠት ልምድ ነውና ሐዋርያት የሠሩትን ጅራፍ ራሱ እንዳበጀው ይናገራል (ትርጓሜ ወንጌል ተመልከት)። ጌታ ያደረገው የሚከተሉት ናቸው።

- ገመድ አበጅቶ በጎችና በሬዎችን እየገረፈ አስወጣ
- ለዋጮችንም (ነጋዴዎች) ገንዘባቸውን አፈሰሰ
- ርግብ ሻጮችንም ከዚህ ውሰዱ ብሎ አባረራቸው

እዚህ ላይ የምናየው ቁም ነገር ጌታ በመዐት እንኳ ቢመጣም ለሚገባው የሚገባውን መስጠት የእርሱ እንደሆነች ማሳያው ነው። ለምሳሌ ርግቦችን ቢገርፍና ቢያስወጣ ርግቦች ይሞቱ ነበር ይህ እንዳይሆን ስለሚፈልግ ግን ለርግብ ነፍስ እንኳ "ርግብ ሻጮችን ይህን ከዚህ ውሰዱ ብሎ ሸኛቸው።" ዮሐ 2፥16 ምንም እንኳ የለዋጮችን ንብረት ቢያፈስ ቢገለብጥ ወይም ገመድን አበጅቶ የሚገፋትን እንስሳት ቢያስወጣ ለሁሉም ንብረታቸውን በተዓምራት መልሶላቸዋል። ከቤተ መቅደስ ውጪ የአይሁድ ክፋት ምን ያህል የምኩራባቸውን ልዕልና አውርደው ከአፈር ደባልቀውት እንደነበር የሚያሳየው ሊሸጡ የመጡትን መቀበላቸው ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም የግብይቱ ማዕከል መሆናቸው ነው። ይህም ማለት ቤተክርስቲያኒቷን ትልቅ የገበያ ማዕከል እንዲሆን አድርገውት ነበር። ለምሳሌ በስጦታ መልክ የሚሰጡ እንስሳትን በግፍ ይለውጡባቸው ነበር። ራሳቸው ምኩራብ ውስጥ በሬ ያሰቡ ያደልቡና በሁለት የከሳ በሬ አንድ የሰባ በሬ ይለውጡና ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ይበድሉ ነበር። በተጨማሪም ራሳቸው አውቀው በሬዎችን እንስሳትን ወደ ምኩራብ ቅጻረ ግቢ እንዲገቡ ያደርጉና "ከሰል አይነጣ ቤተ መቅደስ የገባ አይወጣ" እያሉ እንደተወረሰ አድርገው ንጹሐን ምእመናንን ያስቸግሩ ይረብሹ ነበር። አይደለም የነበራቸውን ሥርዐት ለማስተማር የሚያስችል ዝግጅትና የኀሊና ቆራጥነት ሊኖራቸው ይቅርና ለራሳቸውም በትክክልኛ መንገድ የቆሙ መሪዎች አልነበሩም። በዚህ ምክንያት ቤቱ እንደ ሕግዋ መቆየት ስላለባት በቤቱ ሆነው ሕግ የማይጠብቁትን እንደ ደረጃቸው አስወጥቷቸዋል ገርፏቸዋል ገልብጧቸወል። ይህን እንዳደረገም ደቀመዛሙርቱ በትንቢት የቤትህ ቅናት ይበላኛል ተብሎ እንደተጻፈ አሰቡ። በቤቱ ሲያረጉት የነበሩትን ኢፍትሐዊ ኢሕጋዊ የሆኑ ሥራዎች አንገብግቦት ቤቱን አጸዳ በዚህም ትንቢት ተፈጸመ። መዝ 68፥9 "እስመ ቅንዐተ ቤትከ በልዐኒ ትዕይርቶሙ ለዕለ ይትኤየሩከ ወድቀ ላዕሌየ ወቀጻዕክዋ በጾም ለነፍስየ " ተብሎ ተጽፏል።

**በዕለቱ በቅዳሴ የሚነበብ ወንጌልና ምስባክ**

- ወንጌል ዮሐ 2፥13 - 25
- ምስባክ መዝ 68፥9 - 10
- ቅዳሴ እግዚእ

ይቆየን !

በጥንተ ምሥራቅ ኪዳነ ምሕረት ቤ/ክ
የዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት
ትምህርት ክፍል
ሜሪላንድ